


# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## ለሌሎች መጸለይ ደስታን ይሰጣል

**በቃል የሚጠና፦ 1ኛ ተሰሎ. 5፥16-18**

***"ስለ ሁላችሁም በምጸልይበት ጊዜ ጸሎቴ በደስታ የተሞላ ነው"***
**(ፊልጵስዩስ 1፥4)**

### 1 ጳውሎስ ለደስታው ምክንያት ነበረው

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሚያገለግላቸው ምዕመናን መጸለይ፥ ከአገልግሎቱ ክፍል አንደኛው እንደነበረ በጻፋቸው መልዕክቶቹ መረዳት እንችላለን። በተለይ በፊልጵስዩስ ላሉት አማኞቹ በሚጸልይበት ወቅት ልዩ የሆነ ደስታ እንደሚሰማው ጠቅሷል። ጳውሎስ በዚህ መልዕክቱ ውስጥ ስለ *"ደስታ"* በተለያየ ሥፍራ በመጥቀሱ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የፊልጵስዩስን መልዕት *"የደስታ ደብዳቤ"* ብለው ይጠሩታል። *"ስለ ሁላችሁም በምጸልይበት ጊዜ ጸሎቴ በደስታ የተሞላ ነው"* ይላል (ፊል. 1፥4)። እንዲሁም ወንጌል በመሰበኩ ብቻ ምን ያህል ደስ እንደሚለው ሲገልጽ፥ *"ያም ሆነ ይህ በዚህ ሁሉ ደስ ይለኛል፤ ወደ ፊትም ለደስታዬ ወሰን አይኖረውም፤ ምክንያቱም በመልካምም ሆነ በክፉ አስተሳሰብ በሁሉም መንገድ የክርስቶስ የምሥራች ቃል ይነገራል"* ይላል (ፊል. 1፥18)። ለክርስቶስ ሲል በሚደርስበት መከራም ደስ እንደሚለው ሲገልጽ፥ *"ለእግዚአብሔር በእምነት በምታቀርቡት መሥዋዕትና አገልግሎት ላይ የእኔም ሕይወት ተጨማሪ መሥዋዕት ሆኖ ቢቀርብ እንኳ ደስ ይለኛል፤ እናንተም የደስታዬ ተካፋዮች ትሆናላችሁ። እንዲሁም እናንተ ተደስታችሁ እኔንም የደስታችሁ ተካፋይ ታደርጉኛላችሁ"* ይላል (ፊል. 2፥17-18)።

ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን *"ስለ ሁላችሁም በምጸልይበት ጊዜ ጸሎቴ በደስታ የተሞላ ነው"* ሲላቸው፥ ለማለት ያህል የተናገረው ሳይሆን ከልቡ የተሰማውን ስሜት መግለጹ ነው። የሌሎች ሰዎች ሸክም ተሰምቶን፥ ልባችን በርህራሄ ተሞልቶ እነርሱንና ጥያቄያቸውን ይዘን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ፊት ስንቀርብ፥ ልዩ በሆነ ደስታ ውስጣችን እንደሚሞላ ግልጽ ነው። ጳውሎስ ይህንን ስለተለማመደ ነው *"ስለ ሁላችሁም በምጸልይበት ጊዜ ጸሎቴ በደስታ የተሞላ ነው"* ያለው። ጳውሎስ፥ ለፊልጵስዩስ ምዕመናን ሲጸልዩ ልዩ ደስታ የተሰማው ዝም ብሎ ያለምክንያት አልነበረም። እግዚአብሔር ለፊልጵስዩስ አማኞች ያደረገላቸውን፥ እንዲሁም እነርሱን በመጠቀም የፈጸመን በጎ ነገር ሲያስብ፥ ልቡ በልዩ ደስታ ይሞላ ነበር። ጳውሎስ *"ደስታ"* ሲል ጊዜያዊ የሆነውን፥ ከላይ ብቻ የሚታየውን፥ ወይንም ስሜታዊ የሆነውን ማለቱ ሳይሆን፥ ከልብ የሚፈልቀውን ማለቱ ነው።

### 2 ጸሎታችን ሁሉን ያጠቃልላል?

ጳውሎስ *"ስለ ሁላችሁም"* ሲል፥ ይጸልይ የነበረው፥ ቀረብ ላሉት ለጥቂቶች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም እንደሆነ ሲገልጽ ነው። ቅርባችን ለሆኑት፥ አገልግሎታችንን ለሚወዱና ለሚደግፉን መጸለይ ከባድ አይደለም። መጸለይ ያለብን ለሚወዱንና ለሚደግፉን ብቻ ሳይሆን፥ ሌላው ቀርቶ በመንገዳችን እንቅፋት ለሚያኖሩብንም ጭምር መሆን እንዳለበት የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል። ክርስቶስ ራሱ *"እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ፤ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ስደትና መከራ ለሚያደርሱባችሁም ጸልዩላቸው"* ይላል (የማቴ. 5፥44)። ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ ላመጣቸው ነፍሳችት በጣም የሚያስብ፥ የሚጨነቅና ከልቡ የሚጸልይ ሰው ነበር። ሁሉንም ማቀፍ፥ ሁሉንም ማሰብ፥ ለሁሉም መጸለይ የሚያስችለው ሰፊ ልብ ነበረው። እውነተኛ አገልጋዮች የሚያገለግሉትን ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ይዞ ለመቅረብ የሚያስችል ይህን ዓይነት ሰፊ ልብ ሊኖራቸው ይገባል። የሚያገለግሉት ሕዝብ ሸክም ተሰምቷቸው ያለማቋረጥ መጸለይ አለባቸው። ጳውሎስ ለሚያገለግላቸው ሰዎች የሚሰማውን ስሜት ሲገ

ልጅ፥ *“ልጆቼ ሆይ! የክርስቶስ ባሕርይ በእናንተ እስኪታይ ድረስ እንደገና ስለ እናንተ በምጥ ጭንቅ ላይ እገኛለሁ”* ይላል (ገላት. 4፥19)።

ሐዋርያው ጳውሎስ ከጌታ ጋር ያስተዋወቃቸውን የፊልጵስዩስ አማኞችን ሁሉ በጣም ይወዳቸው ስለነበረ፥ በጸሎቱ ብዙ ጊዜ ያስታውሳቸው ነበር። በወቅቱ በስደትና እንዲሁም በአንዳንድ ሀሰተኛ አስተማሪዎች የተከበቡ በመሆናቸው፥ ስለ እነርሱ በማሰብ በጣም ይጨነቅ ነበር። ይጸልይላቸው የነበረውም ግዴታ ሆኖበት፥ እንደ ሸክም ተሰምቶ ሳይሆን በጣም ደስ ብሎት ነው። ለዚህ ነው *“ስለ ሁላችሁም በምጸልይበት ጊዜ ጸሎቴ በደስታ የተሞላ ነው”* ያላቸው። በወቅቱ ያለ በደሉ ውህኒ ቤት በመጣሉ፥ በብቸኝነቱ ምክንያት የአዕምሮ ጭንቀት ሊያደርስበት የሚያስችል ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም፥ ስለ እነርሱ እያሰበ በሚጸልይበት ወቅት ሁልጊዜ ደስታ ከልቡ እንደ ምንጭ ውሃ ይፈልቅ ነበር።

## 3 ከዚህ ክፍል ውስጥ የምናገኘው ትምህርት

### ሀ እውነተኛ አገልጋዮች ከሆንን፥ ስለ ሌሎች ግድ ይለናል

ለራሳቸው በመጨነቅና በማሰብ ፈንታ ስለ ሌሎች የሚያስቡ፥ የሚጨነቁ፥ ከልባቸው የሚጸልዩ አንዳንድ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን። ከነዚህ መካከል ታሪኩ ብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጻፈው *ነህምያ* አንዱ ነው። በግል ሕይወቱ በጣም የተሳካለት፥ ሁሉ ነገር የሞላለት ሰው ነበር። እርሱ ሳይወለድ የነበሩ ዘሮቹ በእግዚአብሔር ላይ በማመጻቸው ምክንያት እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ግዛት መቅጣቱና ማጥፋቱ የእርሱ ጥፋት አልነበረም። ቢሆንም፥ ከምርኮ የተረፉት ቅሬታዎች በታላቅ መከራ ውስጥ እንዳሉ፥ ኑሮአቸው የመከራና የጭንቀት ሕይወት እንደነበረ፥ የኢየሩሳሌም ቅጥር እንደ ፈረሰ፥ በሮቿ በእሳት እንደተቃጠሉ በሰማ ጊዜ ቁጭ ብሎ እንዳለቀሰ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

### ለ እውነተኛ ያልሆነ አገልጋይ የሚያስበው ስለ ራሱ ደስታ ብቻ ነው

አንዳንድ አገልጋይ ስለ ሌላው ሰው መከራና ጭንቀት መስማት አይፈልግም። የማይፈልግበት ዋናው ምክንያት ኃላፊነት ይኖርበታል ብሎ ስለሚያስብ ነው። የሌላውን ጉዳትና ጉስቁልና መስማት ደስታውን የሚያደፈርስበት መስሎ ስለሚሰማው፥ የሌላውን ችግርና ጭንቀት እንደ ራሱ አድርጎ መውሰድ አይፈልግም። *ነህምያ* ቁጭ ብሎ ያለቀሰው፥ ሩህሩህ፥ ለሌላው የሚጨነቅ ልብ ስለነበረው ነው። *“ይህንንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ቁጭ ብዬ አለቀስኩ”* ይላል (*ነህምያ* 14)።

### ሐ ሳቃችንም ሆነ ለቅሶአችን ማንነታችንን ያሳያል

ሰዎች፥ ለቅሷቸውና ሳቃቸው ማንነታቸውን ያሳያል። የማያስቀው የሚያስቃቸው፥ ወይንም በሌላው ሰው መከራ የሚስቁ፥ እንዲሁም በጥቃቅኑ ነገር ሁሉ የሚያለቅሱ፥ የባህሪ ጉድለት እንዳለባቸው ያሳያል። አንዳንድ ጊዜ ማልቀስ የደካማነት ምልክት ሳይሆን “የብርቱነት” ምልክት ነው። ስለ ሌሎች ስንል የምናለቅሰው ለቅሶ ርህራሄያችንን እንጂ ደካማነታችንን አያሳይም። ለሌሎች ካለቀሱት ሰዎች መካከል አንደኛው ኢየሱስ ነው። ኢየሱስ *“...ከተማይቱን አይቶ አለቀሰላት”* (የሉቃስ ወ. 19፥41)። ለእኔና ለእናንተ እግዚአብሔር ስለ ሌላው ሸክም ሲሰጠን፥ ለመሸሽ አንሞክር። ስለ ሌሎች ማንባትን ችላ የምንል ከሆነ፥ በዕንባ ውስጥ ያለውን በረከት እንዳናገኝ እንሆናለን። ስለ ሌላው የምንጸልየው ጸሎት፥ የምናነባው ዕንባ ምንጊዜም ያለፍሬ አይቀርም። የምናነባለትን ሰው ሕይወት ብቻ ሳይሆን፥ የእኛንም ሕይወት ያለሰልሳል፤ ልባችንንም በደስታ ይሞላል። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ *“ስለ ሁላችሁም በምጸልይበት ጊዜ ጸሎቴ በደስታ የተሞላ ነው”* ያለው። እኛስ ዛሬ እንደ ጳውሎስ ስለምናገለግላቸው ሰዎች ጭንቀትና መከራ ግድ ይለናል? ወይንም ይቆረቁረናል? ሸክማቸው ይሰማናል? ከሆነ፥ ከልባችን እንጸልይላቸው።




**የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።**

(ትንቢተ ኢሣ. 40፥8)




## ሀ የመልእክቱን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የፊልጵስዩስን መልዕክት ምን ብለው ይጠሩታል?

2. ይህን ስም የሰጡበት ምክንያት ምንድነው?

3. ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ሲጸልይ የሚሰማው ስሜት ምን ዓይነት ነበር?

4. ይህን ዓይነት ስሜት የተሰማው ምክንያቱ ምንድነው?

5. ለሚወዱን ብቻ ሳይሆን ለሚጠሉንንም ጭምር መጸለይ እንዳለብን በምን እናውቃለን? (የማቴ. 5፥44)

6. ጳውሎስ ለሚያገለግላቸው ሰዎች የሚሰማውን ስሜት ሲገልጽ ምን ይላል? (ገላት. 4፥19)

7. ጳውሎስ ይጸልይ የነበረው ለአንዳንዶች ብቻ እንዳልነበረ በምን እናውቃለን? (ፊልጵ. 1፥4)

## ለ በዚህ ክፍል ውስጥ ያገኘነውን ትምሕርት በግል ሕይወታችን ለመለማመድ...


1. ጳውሎስ ለሚያገለግላቸው ምዕመናን መጸለይ፥ ከአገልግሎቱ ክፍል አንደኛው ነበረ። እኛስ ለምናገለግላቸው ምዕመናን እንጸልይ ይሆን? እንዳንጸልይላቸው ዕንቅፋት የሚሆኑብን ምክንያቶች ምንድናቸው?

2. “ለቅሷችንና ሳቃችን ማንነታችንን ያሳያል” ስንል፥ ምን ማለታችን ይሆን?

3. ስለ ሌሎች በማሰብ ከተጨነቁትና ካለቀሱት ሰዎች መካከል አንደኛው ነህምያ ነው። እኛስ የምንጨነቅላቸውና የምናለቅስላቸው ሰዎችና ሁኔታዎች ምንድናቸው?

4. ክርስቶስ ክፉ ያደረጉበትን ይቅር ማለት ብቻ ሳይሆን፥ እንደጸለየላቸው እናውቃለን። እኛስ ለሚጠሉን ሰዎች እንጸልያለን? ካልሆነ መውሰድ ያለብን እርምጃ ምንድነው?

5. የጸሎት ሕይወታችን እንዴት ነው?



የትምሕርቱ አዘጋጅ
መለሰ ወጉ

# ስንቅና ትጥቅ

በኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ተዘጋጅቶ፥ በየሁለት ሳምንቱ እየታተመ የሚወጣ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው።

**Ethiopian Outreach Ministry**
**P.O.Box 2241**
**York, PA 17405**
**U.S.A.**
**Phone/Fax: (717)846-2041**
**E-Mail: eomusa@aol.com**
**Internet Address:**
**www.ethiopianoutreach.com**

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አድራሻ